# ህወሓትን ከጭቁኑ የትግራይ ህዝብ ነጥሎ መታገል

ክፍል አንድ ከባርናባስ ገብረማሪያም

አንጋፋው ኢትዮጵያዊው ምሁር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያ ሰሞኑን በተለመደው አንደበተ ርቱዕ ብዕራቸው በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ውስጥ የተከሰተውን የፓለቲካ ቀውስ አስመልከተው የሁላችንም የልብ ትርታ የሚነካ ወቅታዊና አንገብጋቢ የሆነ ጥናታዊ ፅሑፍ አቅርቧል:: ፅሑፋቸውን አንብቤ ጠቅለል ባለመልኩ እንደተረዳሁት በሀገራችን ውስጥ ያለውን አስፈሪ ሁኔታ አፋጣኝና ዘላቂ መፍትሄ ካልተገኘለት ውሎ አድሮ መዘዙ ምን ሊሆን እንደሚችል በማያሻማ መልኩ በተለይም ለትግራይ ህዝብና እንዲሁም ለስርዓቱ ተዋናዮች በሙሉ ግልፅ የሆነ መልእክት በማስተላለፍ <u>ልብ ያለው ልብ ይበል</u> ብሏል:: ያወጡትን ባለአስር ገፅ ፓለቲካዊ ትንተና ከወትረው ለየት ባለ መልኩ አንድ እርምጃ ወደፊት በመሄድ አስበውበትና ከብዙ ምሁራኖች ጋር ተወያዩተውበት ያስቀመጡት ጥናታዊ ፅሑፍ ነው ብዬ እገምታለሁ:: ፅሑፉ ለውይይት የሚጋብዝ በር ከፋችና አቅጣጫ ጠቋሚ ከመሆኑም በላይ ወቅታዊና ሚዚናዊ ነው:: ስለዚህ የፃፉትን ፅሑፍ መነበብ ያለበት ብቻ ሳይሆን መጠናከርም ያለበት ነው ብዬ አምናለሁ:: በበኩሌ ይህንን አጭር ፅሑፍ ብድግ ብዬ እንድጭር ከገፋፉኝ ምክንያቶችም አንዱ የሳቸውን ፅሑፍ ካነበብኩ በኋላ ነው:: አዎ! ሳይጨልም አይነጋም እንዲሉ አንዳንድ ታላላቅ ሰዎች የሚናገሩትን ራዕይና ትንቢት ጊዜውን ጠብቆ ህያው ሆኖ የሚገኝበት ዕድል ብዙ ነው::

ተደጋገሞ እንደተባለው ህወሓት ነፃ አውጪ ነኝ እያለ በትግራይ ህዝብ ስምና ደም እየነገደ ፤ ትግራይን መረማመጃና መደበቂያ ዋሻ አድርጎ እየተጠቀመ ፤ የትግራይ ተወላጆችን አጃቢና አገልጋይ አድርጎ ከጎኑ እያሰለፈ ፤ እንዲሁም የአግኣዚ ጦር ሰራዊትን የቂም በቀል መወጣጫ መሳሪያ አድርጎ በየክልሉ በማሰማራት በሌሎች ንፁሃን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ላይ እያደረሰ ያለውን እልቂትና እንዲሁም በየቀኑ በተለያዩ ከተሞች በጭካኔ እየፈሰሰ ያለውን የለጋ ወጣቶቹን ንፁህ ደም ተጠያቂው ማን ነው? ሁኔታው በዚሁ ከቀጠለ ደግሞ በሀገራችንና በህዝባችን ህልውና ላይ ሊያስከትለው የሚችል መዘዝ ምንድን ነው? መፍትሄውስ ምን ሊሆን ይችላል? ለሚለው አንገብጋቢና ወቅታዊ ጥያቄ ፕሮፌሰሩ በጥሩ አማርኛ ከነመፍትሄው በቂ መልስ አስቀምጧል::

አዎ!! ለተፈጠረው ጥፋትና ቀውስ በተለይም ሐቁንና ውሸቱን ምርቱንና እንክርዳዱን ህዝቡንና ዓፋኝ ስርዓቱን ለይተው ማየት ያቃታቸው ፤ ዓይናቸውን በፍቅረ ንዋይና በስልጣን ጥም ታውሮ የንፁሃን ዜጎቻችንን ጭኾትና ደም የዶሮን ያህል ግምት የማይሰጡ ፤ አስተሳሰባቸውና ተግባራቸው ሁሉ ገና ከተፈጠሩባት ቀን ጀምሮ በዘር ጥላቻና ምንቀኝነት ተኰትኩተው ያደጉና አእምሯቸውን በጠባብ ፓለቲካዊ እምነት የተወቀሩ ፤ ጊዜና ሁኔታ የማይለውጣቸውና አሁንም ገና በደደቢታዊ የጫካ ቋንቋ የሚዘምሩና በጫካ ሕግ የሚያስተዳድሩ ፤ ዘረኝነትን እንደ ወባ በሽታ በደማቸው ውስጥ ሰርፆ በመግባት ከህዝባቸው ጋር ከመወገንና ጥብቅና ከመቆም ይልቅ የጥቂት መሪዎችን አገልጋይ ሆነው ለመኖር የመረጡና ህወሓትን እንደ ጣዖት የሚያመልኩ ፤ በአጠቃላይ ለአርባ ዓመታትን ያህል ለራሳቸው ነፃ ሳይወጡ ነፃ አውጪ ነን እያሉ በሰማእታቱና በጭቁኑ የትግራይ ህዝብ ስም የውሸት ደራማ ሲሰሩ የኖሩና አሁን አማራጭ መንገዱ በማጣት ቀኑ የመሸባቸው <u>የህወሓት መሪዎች፣ ካድሬዎቻቸው፣ አባላቶቻቸውና ደጋፊዎቻቸው ናቸው ተጠያቂዎቹ</u> ::

ዛሬ ምርቱንና እንክርዳዱን ለይተን እንታገል ሲባልም እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን <u>እሾኽ አሜኬላዎች</u> ከጭቁኑ የትግራይ ህዝብ ነጥሎ ለመታገል የሚያስችል አመለካከት፣ ዓቅምና የትግል አንድነት መፍጠር አማራጭ የሌለው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው:: በሀገር ደረጃ ነፃነትና ፍትሕ ከሌለ በምንም መልኩ የትግራይ ህዝብ ለብቻው ተነጥሎ ሰላምና ፍትሕ ማግኘት እንደማይችል እኖሆ ዛሬ በሀገሪቱ እየታየ ያለው እውነታ ያስረዳናል:: ስለዚህ እንደ ፕሮፌሰሩ አገላለፅ የትግራይ ህዝብ ያሉት አማራጮች ሁለት ናቸው:: አንዱ አማራጭ የህወሓትን ጉዞ የጥፋት ፣ የእልቂት፣ የመበታተንና የባርነት ጉዞ መሆኑን በውል ተገንዝቦ ከሌሎቹ ወንድሞቹ ጋር የትግል አንድነቱን በማጠናከር ራሱንና ሀገሩን ማዳን ነው:: ሁለተኛውና ሁላችንም የማንፈልገው አማራጭ ደግሞ በመከሰም ላይ ከሚገኘው ጨቋኝ ስርዓት ጋር ወግኖ ዙሪያውን ሁሉ በጥላቻ አጥሮ ማለቂያ በሌለው ቅራኔ ተዘፍቆ መኖር ነው:: ስለዚህ ወደድንም ጠላንም ለሁላችንም የሚበጅ አማራጭ መንገድና መፍትሄ መፈለግ የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ግዴታና ሃላፊነት ሆኖ ይገኛል::

የኢትዮጵያ ህዝብ ህወሓትን ከማንም በላይ እንደ ደመኛ ጠላቱ አድርጎ የሚያይበት መሰረታዊ ምክንያት ምንድን ነው? ለሚለው ዓቢይ ጥያቄ ለመመለስ የግድ የፓለቲካ ምሁር ወይም ተመራማሪ መሆንም የሚጠይቅ አይደለም:: ማንኛውም የህዝብ ወገን የሆነና ሀገሩን የሚወድ ሰው ሁሉ በቀላሉ ሊገልፀውና ሊረዳው የሚችል የህልውና ጉዳይ ነው:: ህዝቡ እየጮኸ ያለውም ህወሓት አጥፍቶ ከመጥፋት ይልቅ መንገዱን አስተካክሎ ልኩን አውቆ እንዲኖር አሊያም በህዝባዊ ዓመፅ እንዲወገድ የሚፈልግበት ዋናው ምክንያት በቋንቋው ወይም ከትግራይ ስለመጣ ሳይሆን ልክ እንደ ደርግ ስርዓት ጨቋኝ ስለሆነ ብቻ ነው:: ቅራኔው ከትግራይ ህዝብ ጋር አይደለም:: የትግራይ ህዝብማ ከህወሓት በፊትም የነበረ ያለና ለወደፊትም የሚኖር ማንም የማይቸረው ደሙን ከፍሎ ያቆያትን ሀገር ባለቤት ነው:: ስለዚህ የዓመፁን መነሻና አቅጣጫ ህወሓቶች እንደሚሉት በህዝቡ ላይ ያነጣጠረ ሳይሆን ላለፉት አርባና ሃምሳ ዓመታት በአንድ አምባ ገነናዊና ሞኖፓላዊ አገዛዝ ስር ወድቆ ማለቂያ የሌለው የባርነት ቀንበር ተሸክሞ የሚገኝ ህዝብ የሁሉንም ጭቆናና ዓፈና ምንጭ ህወሓት መሆኑን በማያሻማ መልኩ አበጥሮ

ስለሚያውቅ ነው። በመሆኑም በአንድ በኩል የህዝቡን ምሬትና ጭኾት በሌላ በኩል ደግሞ የስርዓቱን አረሜናዊ ባህርይና እኩይ ተግባር ገፅ ለገፅ ስናስተያየው ህዝቡ ህወሓትን እንደ ዲያብሎስ አድርጎ የሚያይበት መሰረታዊ ቅራኔው ምን ላይ እንደተመሰረተ የሚከተሉትን አስር ነጥቦች ማየቱ ብቻ በቂ ይመስለኛል።

1. ህወሓት የህዝብን አደራ የበላና ሀገሩን የሸጠ ከሐዲ ድርጅት ነው
2. ህወሓት በውሸትና በተንኰል የተካነ አሸባሪና ነብሰ ገዳይ ድርጅት ነው
3. ህወሓት በህዝቡ መካከል ፀረ ኢትዮጵያዊነት መርዝ የዘራ ከፋፋይ ድርጅት
4. ህወሓት የሀገርና የህዝብ ፍቅር የሌለው የባዕድ መሳሪያ ድርጅት ነው
5. ህወሓት ፀረ ዕድገትና ፀረ ልማት የሆነ ዘራፊ (ሙሰኛ) ድርጅት ነው
6. ህወሓት የሰላም የፍትሕ የነፃነት የዴሞክራሲና ያንድነት ነቀርሳ ነው
7. ህወሓት ርህራሄ የሌለው የሰብአዊ ፍጡር ደመኛ ጠላት ነው
8. ህወሓት በሰማእታት ስምና በትግራይ ህዝብ ደም እየነገደ የሚኖር አታላይ ድርጅት ነው
9. ህወሓት በአፈ ሙዝ የነገሰና በአፈ ሙዝ እየገዛ የሚገኝ አምባ ገነን ቡድን ነው
10. ህወሓት ሀይማኖት የሌለው ፣ ሕግ የማይገዛው ፣ ታሪክ የማይገታውና ባህል አልባ የሆነ የወሮ በሎች ድርጅት ነው

ዛሬ ህወሓት በህዝብ የተተፋ ስርዓት መሆኑን ራሳቸው የህወሓት ቁንጮም ሳይቀር ስርዓታቸው በህዝብ ዘንድ እንደተጠሉና እንደከሐዲ እንደሚታዩ በይፋ መናገር ጀምሯል። ለምሳሌ በቅርቡ ከ3000 በላይ ካድሬዎችና መሪዎቻቸው የተሳተፉበት በመቀሌ በተካሄደውን የነብስ አድን ስብሰባ ላይ አቶ ስዩም መስፍን " ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮኋል" እንዲሉ ለአርባ ዓመታትን ያህል ስልጣን ላይ ተቀምጦ ቅንጣት ታህል የዴሞክራሲ ለውጥ ያላመጣ ዛሬ ባለቀ ሰዓት ላይ ሆኖ የአዞ እንባ እያነባ "ህዝቡ የታገለለትን አላማ ተግባራዊ ሳይሆን ስለቀረና ለህዝቡ የገባንበትን ቃል ኪዳን ስላልተጠበቀ ህወሓትን እንደከሐዲና እንደጠላት እያየን ነው። ስለሆነም የህዝቡን እንባ ሳናደርቅና ወጣቱን ከያዘው የጥፋት መንገድ መልሰን የስርዓታችን ተጠቃሚና ደጋፊ ሳናደርግ ቀኑ እንዳይመሽብን እሰጋለሁ። ስለዚህ አሁን ከእንቅልፋችን ነቅተን የተደገሰልንን ጥፋት ቀልብሰን ወደፊት ለመራመድ እጥፍ ድርብ ሩጫ መሮጥ አለብን" በማለት እንደልማዱ አስፈሪና አስደንጋጭ በሆነ አገላለፅ ህወሓትን ከሞት እናድን ሲል ተደምጧል። የአቶ ስዩምን ንግግር ስሰማ አንድ የቅርብ ጓደኛዬ ወደ ኢትዮጵያ ሂዶ አንድ የዕድሜ ባለፀጋ አዛውንት ሲናገሩ የሰማውን እንዲህ ሲል አጫውቶኛል " <u>ደርግ ሰው ገድሎ በአደባባይ አካኪ ዘራፍ ይላል-ህወሓት ግን ሰው ገድሎ ልቅሶ ይደርሳል</u>" የሚል ነው። እርግጥ ነው፡ ዛሬ እየተደረገ ያለው የህወሓት መሪዎች አስቂኝና አሳኝ ድራማም የአዛውንቱን አባባል በትክክል የሚገልፅ ነው።

ህወሓትን ከጥንስሱ እስከ ድግሱ ከፍተኛ የአማራር አባል በመሆን ሲታገሉ ከነበሩት ውስጥ ዛሬ የአረና ትግራይ መድረክ የማእከላይ ኮሚቴ አባል የሆኑት አንጋፋው ምሁር አቶ ገብሩ አስራት በቅርቡ በአማርኛ "ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵዮያ " በሚል ርእስ የፃፉትን ግዙፍ መፅሐፍና እንዲሁም ዶክተር አረጋዊ በርሀ በእንግሊዝኛ ያሳተሙት ("The political History of The TPLF – 1975 -1991") የሚል መፅሐፍ ልብ ብላችሁ ያነበባችሁት ሰዎች ካላችሁ ህወሓት ምን ዓይነት ድርጅት እንደሆነ ትስታላችሁ የሚል እምነት የለኝም። ከዚህ በተጨማሪም በህወሓት የትጥቅ ትግሉ ዘመን የከፍተኛ አመራር አባልና የድርጅቱን ወታደራዊ ኮማንደር ፣ በኋላም የመከላኪያ ሚኒስተር የነበረው አቶ ስየ አብርሃም እስር ቤት በነበረበት ጊዜ ያየውና የሰማውን ሲናገር "በኢትዮጵያ ያሉት እስር ቤቶች ሁሉ ኦሮሞ ኦሮሞ ይሸታሉ። በየቀኑ እኩለ ሌሊት ሲሆን በእስረኛው አካባቢ የሰው ጭኾትና ልቅሶ መስማቱ የተለመደ ነብር" በማለት ገልፀዋል። የአንድነት ፓርቲ የአመራር አባል የነበረውና ዛሬ በስደት ዓለም የሚገኘው አቶ ሀብታሙም በእስር ቤት በነበረበት ጊዜ የደረሰበትን የቂም በቀል በደል ምን ያህል ዘግናኝና አሰቃቂ እንደነበር በፅሑፍ ከትቦ ለትውልድ ምስክርነት አቅርቧል። ሰሞኑን ፐ/ር መስፍን ለንባብ ያበቁትን ጥናታዊ ፅሑፍና እንዲሁም ሌሎቻችሁ በተለያየ አጋጣሚ በብዕርም ሆነ በቃል የገለፃችሁትን ሁሉ ተደምረው የስርዓቱን ፀረ ህዝብነትና ፀረ ኢትዮጵያዊነት ተግባር የሚናገሩ ህያው ምስክሮች ናቸው።

የኢትዮጵያ ህዝብ የዋህ ፣ ይቅር ባይና ታጋሽ የመሆኑን ያህል ለመሪነትና ለሰላም ግን አልታደለም። ህወሓቶች ሬሳ በሬሳ እየተረማመዱና የሀገርን ሀብት እያወደሙ አዲስ አበባ ሲገቡ ህዙቡ ምናልባት ከደርግ ይሻሉ ይሆናል ብሎ በማሰብ በጠላትነት አላያቸውም ነበር። "ትናንት ከባዕድ ሀይል ጋር አብራችሁ ዳር ድንበር ለመጠበቅ የዘመቱትን ልጆቻችን ስትገድሉ የነበራችሁ እናንተ ናችሁና አንቀበላችሁም አላለም። ትናንት ከሻዕቢያ ጋር አብራችሁና ተመሳጥራችሁ ሀገራችንን ሽባ ያስቀራችሁና ብሄራዊ ጥቅማችንን ለባዕድ አሳልፋችሁ የሸጣችሁት እናንተ ናችሁና አንቀበላችሁም አታስተዳድሩንም አላለም። ደደቢት ገብታችሁ የታገላችሁት ትግራይን ነፃ ለማውጣት እንጂ እኛን ነፃ ለማውጣት አይደለም። ስለዚህ የትግራይ ነፃ አውጪ ነን እያላችሁ እኛን መግዛት አትችሉም አላላቸውም። የትግራይ ነፃ አውጪ ነን እያላችሁና በትግራይ ህዝብ ስም ዙፋን ላይ ተቀምጣችሁ ነገር ግን እኛን እየጠላችሁና እየረገጣችሁ መግዛት አትችሉም ውጡልን አላላቸውም። እንዲያውም እነሱም በሀገርና በህዝብ ላይ ለፈፀሙት ግፍና ክሕደት ተንበርክከው ህዝቡን ይቅርታ መጠየቅ ሲገባቸው በተገላቢጦሽ ህዝቡ ነው የይቅርታ መንፈስ ያሳያቸው። ነገር ግን የህዝቡን የዋህነትና ታጋሽነት እንደበጎ ሳይሆን እንደፍርሃት በመቁጠር የገዛ ወንድሞቻቸውን እየገደሉ ስለመጡ ብቻ እነሱ በተፈጥሯቸው ጀግኖች ሌላ ህዝብ ግን ፈሪና ምርኮኛ ፤ እነሱ የሀገርና የስልጣን ባለቤት ሌላው ህዝብ ግን የእነርሱ የስልጣን ተስፈኛና ተመፅዋቾች ፤ እነርሱ ነፃ አውጪ ሌላው ህዝብ ግን ሀገሩንና መብቱን ማስከበር የማይችል ሽባ

አድርገው በመቁጠር የልብ ልብ ተሰምቷቸው ከህዝብ ከሀገርና ከሕግ በላይ በመሆን በአፈ ሙዝ እየኰረኰሙ መግዛት ከጀመሩ እኖሆ አሰርቱ ዓመታትን በማስቆጠር አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

የዙሁ ሁሉ ድምር ውጤትም አሁን ሀገራችን ያለችበት ሁኔታ ስናይ ህዝቡ የደርግ የቀይ ሽብር ቁስሉ ገና ሳይሽርና ከአእምረው ሳይፋቅ ዛሬም ሀገራችን ዋይታና ልቅሶ  የነገሰባት ፣ የነገ ሀገር ተረካቢ የሆኑትን ለጋ ወጣቶች በአልሞ ገዳይ እየተቀጠፉ ተሰፋው የጨለመባትና ባለቤት ያጣች ሀገር ሆና ስናያት እጅግ ያሳዝናል።

ይህ ሁሉ መቋጫ የሌለው ስቃይና መከራ ስመለከት ሁሉ ጊዜ በአእምሮዬ የሚመላለሱ ጥያቄዎች አሉ። እነሱም ህወሓቶች የህዝቡን ሉዓላዊ ክብርና የሕግ የበላይነት አክብረው ተግባብተው በሰላም መኖር እየቻሉና ለነርሱም ጭምር የሚጠቅም መሆኑን እያወቁ ለምን የጥፋት መንገድን መረጡ?  ለምን የፓለቲካ ምሕዳሩን ማስፋትና ነፃ የዴሞክራሲና የፍትሕ ተቋማትን እንዳይኖሩ ይፈራሉ? ፍትሕ ከሌለ ሰላም እንደማይኖር ጠንቅቀው እያውቃሉ ለምን ከታሪክና ከተመኩሮ አይማሩም።? ህወሓት የሚመራውን መንግስት ከደርግ ስርዓት የማይማርና የማይሻል ከሆነ ለምን ቀድሞውንስ ቢሆን ወደ ጫካ ገቡ።? የሚሉና በሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በሚቀጥለው ክፍል ሁለት ፅሑፌን በዝርዝር ለማቅረብ እሞክራለሁ - ሳምንት እንገናኝ።